ቁጥር፡ OFAGF-03.3/1/18
ቀን 09/06/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ዶ/ር ፍፁም አሰፋ

የብሔራዊ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የ2011 በጀት ዓመት</u>

<u>ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

በየነ ኑሪ
ፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክተር
Finance & Communication Oranization
Audit Director

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ
  (ከ9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ፣
  የስራ አመራር ሪፖርት 57 ገጽ
  እና 13 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች ጋር)
  <u>አዲስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የካቲት/ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶችን ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የሪከርድና ማህደር
መ/ቤት

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ወጪ ሂሳብ

   1. **የጥሬ ገንዘብ ጉድለት**

      የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር ከ1-8 እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተራ ቁጥር 4 ላይ መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፣ መመሪያው ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ገንዘብ ከመከፈሉ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውን ቅድመ ጥንቃቄዎች ተከትለው የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሁለት ሰራተኞች ላይ በድምሩ ብር 37,705.55 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት መገኘቱ ፣

   2. **የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ**

      የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እና የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟለ ማስረጃና ለተገዛ ዕቃ ኦሪጅናል ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

      - ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የኢንትግሬትድ ሳይበር ሴኩሪቲ ዳሰሳ አገልግሎት ግዥ ብር 11,721,203.68 ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከተመዘገበው ሂሳብ ውስጥ ብር 141,278.68 ዋጋ ያላቸው የግዥ ሰነዶች (Original invoice) ለኦዲት ያልቀረቡ መሆኑ፡፡
      - በኤጀንሲው የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የእቃና አገልግሎት ግዥ መጠየቂያ እና መፍቀጃ ሳይሞላ ብር 87,000.00 ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

- ብር 2,047,382.24 በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለስልጠና አገልግሎት ወጪ የተደረገ ቢሆንም የተሳታፊዎች የስም ዝርዝር እና በስልጠናው ላይ ለመገኘታቸው በሰልጣኙ ፊርማ የተረጋገጠ የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ከወጪ ማስረጃው ጋር ሳይያያዝ በወጪ የተመዘገበ በመሆኑ ክፍያው ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፡

3. <u>ትክክለኛ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 በክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣው ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይተው በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ኤጀንሲው በመመሪያው መሰረት እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡- ብር 2,513.74 በሂሳብ መደብ 6213 (ለህትመት) አገልግሎት የሂሳብ መደብ መመዘገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6259 (ለውሃና ለሌሎች አገልግሎቶች) ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፣

4. <u>ቅድመ ታክስ (Withholding tax)ያልተቀነሰለት ሂሳብ</u> ፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ክፍል 6 አንቀፅ 24 ተራ ቁጥር 1 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፅም እንዲሁም በአንድ ጊዜ ግዥ ከብር 10,000.00 በላይ ክፍያ ሲፈፅም 2% (ሁለት በመቶ) ዊዝሆልዲንግ ታክስ ቀንሶ በማስቀረት ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ /ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን/ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ይሁን እንጂ የኤጀንሲው የሀረር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ ብር 6,382.61 ዊዝሆልዲንግ ታክስ ቀንሶ ያላስቀረ መሆኑ፣

5 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u> ፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ቁጥር 4/ለ/ መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 16 ቁጥር 4 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ

እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ፡- በሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ ፡-

- የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 1 (ሠ-3) በመንግስት መስሪያ ቤቶች ከተያዙ ሌሎች ፕሮጀክቶች በጀት በማዛወር ለአንድ ፕሮጀክት መጠቀም እንደማይቻል የተገለጸ ቢሆንም ኤጀንሲው በሂሳብ መደብ 4274 ብር **5,833,187.62** ከ2004 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በ14 የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚፈለግ ተብሎ በመደበኛ በጀት በተሰብሳቢ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን ተሰብሳቢው የሚሰበሰብ ለመሆኑ አስቀድሞ ያልተረጋገጠ ከመሆኑ በተጨማሪ ረጅም ጊዜ የሆነው በመሆኑ የመደበኛ በጀት የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት አላግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ የተደረገ መሆኑ፤

- በሂሳብ መደብ 4274 ከአምስት ዓመት በላይ የቆየ ብር 526,545.45 በተሰብሳቢ ተይዞ ቆይቶ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰብሰብ የተጀመረ ቢሆንም ከመስከረም 1/2010 በኋላ የተቋረጠ መሆኑ ፡

- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች በድምር ብር **917,101.33** በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚፈለግ ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ከጊዜው ቆይታ አንጻር የሰነድ ማስረጃ የሌለው መሆኑ፤

- ብር 10,952.15 በጥቅል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የሚፈለግ ተብሎ በኢፍሚስ ሲስተም ምዝገባ ላይ የሚታይና የሚጣራ በማለት የተያዘ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑ፡

በአጠቃላይ ብር 7,287,786.55 ሳይሰበሰብ የቆየ በመሆኑ ተሰብሳቢነቱ አጠራጣሪ ከመሆኑም በላይ የመሰብሰብ እድሉ የመነመነ በመሆኑ የተሰብሳቢ ሂሳብ አላግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ መሆኑ፡

5. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ፤</u>

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት በኤጀንሲው የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ብር 1,945,147.32 ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር አምስት ዓመት ሳይከፈል የቆየ በመሆኑ ለባለመብቱ የመከፈል እድሉ የመነመነ መሆኑና ሂሳቡ ተጣርቶ ከመዝገብ እንዲሰረዝ አለመደረጉ፣
- ብር 239,224.67 ከዊዝ ሆልዲንግ እና ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ላይ የተሰበሰበው ታክስ ከዓመት በላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ (ለገቢዎች ሚኒስቴር) ገቢ ያልተደረገ መሆኑ ፣
- በሂሳብ መደብ በ5061 ላይ የሚታየው ብር 26,312.59 የመያዣ ሂሳብ ከ2007-2010 ድረስ በተከናወኑ ግዥዎች ላይ የተቆረጠ ገንዘብ ሲሆን ስራው የተጠናቀቀ ቢሆንም ጉዳዩ ተጣርቶ ክፍያ እንዲፈጸም እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት የዘገየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5002፡5027፡5028፡እና 5054 በድምሩ ብር 1,394,924.01 ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የቆየና በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ መሆኑ፡

በአጠቃላይ ብር 3,605,608.59 ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ባለመከፈሉና የመከፈል እድሉ የመነመነ በመሆኑ የተከፋይ ሂሳብ አሳግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገው መሆኑ፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የኤጀንሲው የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶቹ በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት የተዘጋጁ በመሆናቸው በእኛ አስተያየት አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የፋይናንሻል ኦዲት
መ/ቤት

ሌሎች ጉዳዮች

ምንም እንኳን ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. **ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት**

   የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር አንድ ላይ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁንና ኤጀንሲው የተደለደለለትን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ በ2011 በጀት ዓመት ለኤጀንሲው ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዋና ዋና የበጀት አርዕስቶች ከ10% (በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የመደበኛ በጀት ብር 4,329,373.40 እና የካፒታል በጀት ብር 796,639,660.33 በድምሩ ብር 800,969,033.73 ከ10% 9 በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መገኘቱ፤

2. **የንብረት አስተዳደር**

   የኤጀንሲው የንብረት አስተዳደር በንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም በፌደራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ተግባራዊ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

   በዋና መ/ቤት

   - ኤጀንሲዉ ለህዝብና ቤት ቆጠራ የተገዙ ታብሌቶች በንብረት ቆጠራ ዉስጥ ያልተካተቱ እና ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት ያልተደረጉ መሆኑ፣
   - ለቅርንጫፎች የተከፋፈሉት ታብሌቶች በወቅቱ ያልተመለሱ በመሆናቸው ምን ያህል እንደጎደለና በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የማይታወቅ መሆኑ ማለትም ንብረቶቹ በቀላሉ ሊበላሹ ወይም ሊሰረቁ የሚችሉ እንደመሆናቸዉ መጠን ተገቢዉን የሆን ቁጥጥር እየተደረገ አለመሆኑ፣
   - በኤጀንሲው በግምጃ ቤት ዉስጥ ለህዝብ እና ቤት ቆጠራ ተብለው የተገዙ ታብሌቶች ከነ ፓወር ባንካቸው (power bank) ሲንካርድ እና ስቶር ካርድ ሳይሰራላቸዉ የተቀመጡ መሆኑ፤

- ታብሌቶች 1 window based regged tablet ፣ 1 tablet,trimble ፣ እንዲሁም 4 Samsung galaxy tap ፣, 44 lenavo thinkpad ፣,3 dell latitioude tablet፣ ዋጋ የሌላቸዉ መሆኑን ፣
- በኤጀንሲው ከህዝብ እና ቤት ቆጠራ ውጪ በተለያዩ ግዜያት ሲገለግልባቸው ከነበሩት ታብሌቶች ውስጥ 260 Lenovo ታብሌት ፣ 208 huawel ታብሌት ፣ 13 cope computerT561፣ 4 cope computer T350 ፣, 89, tecno drowpad tablet ፣ 7,እንዲሁም projector ፣ 7, digital mizan፣ 12 dell computer ፣ 2 tosheba ፣ 8 lenevo computer ፣ እና 91 mouse ፣ አገልግሎት የማይሰጡ ወይም ተጠግነዉ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸዉ በባለሞያ ሳይረጋገጥ አንድ ላይ ተከማችተዉ የተቀመጡ መሆኑ፣ እና በተጨማሪ የተለያዩ ብዛታቸው 7 ዴል ኮምፒውተሮች፣ 9 dell system unit፣ 2 Comac computer፣ 2 hp system unit፣1 flat hp computer፣ 1 Dell flat computer፣ 3 ሶፋ፣ 11 የብረት መደርደሪያ፣ 67 የችርቻሮ ሚዛን፣ 1 Lexa mark(ኮፒ ማሽን)፣ 13 ፋይል ካብኔት፣ 15 የእንጨት መደርደሪያ፣ 31 ወንበሮች፣ 6 የስብሰባ ጠረጴዛ፣ 7 የጠረፔዛ መስታዎቶች፣8 የተሽከርካሪ ጎማ፣2 ጄኔሬተር ያለ አገልግሎት በንብረት ግምጃ ቤት (Store) ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑን,
- አገልግሎት የማይሰጡ እና የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን 1 ላንድ ክሩዘር መኪና፣ 1 ኒሳን ፓትሮል፣ 2 ፎርድ ፒካፕ እና 1 ቶዮታ ፒካፕ በአጠቃላይ 5 መኪናዎች በእርጅና ምክንያት ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ ሲሆን በመሆኑም ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ከሆነ ጥገና ተደርጎላቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ያልተደረጉ መሆናቸው እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በሚመለከተው አካል እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑን ታውቋል፡፡

<u>በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ንብረት አስተዳደር</u>

- በግምጃ ቤቱ ውስጥ በቁጥር 4 Asses እና 3 Tecno tablet ቢን እና እስቶክ ካርድ ሳይኖራቸው በንብረት ክፍል በሳጥን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የንብረት የገቢ እና ወጪ ተግባር (ስራ) በአንድ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ ፣
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ጎማዎች አገልግሎት ከማይሰጡ የመኪና ተመላሽ ጎማዎች ጋር ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

- በግምጃ ቤቱ ውስጥ በርካታ የተለያዩ ዕቃዎች ለቆጠራ ዕና ለዕይታ በማያመች መልኩ ተቀመቀጠው የሚገኙ ከመሆኑም በላይ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉትና የማይችሉት ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ፤

- ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማሰጡ 2 ኮፒይ ማሽን 8 ዴስክ ቶፕ፤ 68 ሽራ ድንኳን፤ 2 ፕሪንተር 110 ሚዛን ከነሳጥኑ ፤ከ 300 በላይ calculater፣ ዣንጠጥላ ፣ ስሊፕ ባግ እንዲሁም የተለያዩ ቻርጀሮች በንብረት ክፍል ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- 4-07910 ኢት የሆነች ኒሳን ፓትሮል የሀነች መኪና ከሁለት ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት በጊቢ ውስጥ ቆማ ያለች መሆኑ ፣

በተወሰኑት ክፍተቶች ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ባሉበት ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል ።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት